በት የሠርግ ቤት በእጅጉ የባሰ ችግር ነው ። ምክንያቱም የሕይወት ጉዳይ ነውና ። የሠርጉ ባለቤት ያለቀበት ወይን ነበረ ። የዛሬ ሰው ግን ያለቀበት ክርስቲያናዊ ሥርዐት ፣ ሞራላዊ ሕይወትና ቁራጥ ወኔ ነው ።

በሥርዓት ትዳር ለመሠረቱት ጌታ በረከቱን ለመስጠት ገና በሠርጉ ዕለት ጀመረ ። ይህም በረከት እስከ ሕየወታቸው መጨረሻ ድረስ የሚቀጥል መሆኑን ያመለክታል ። ይህ ያልገባቸው ሰዎች ግን እግዚአብሔር ሕይወታቸውን እንደሚመራ ስለማያምኑና ስለሚጠራጠሩ የሚጨብጡት አጥተው ከትዳር ዓለም ርቀው ይቀራሉ ። ይህ እንዳይሆን ሕገ እግዚአርሔርን መጠበቅ ተገቢ ነው ።

በጋብቻ ዝግጅት ጊዜ እንደ ሌላው ዝግጅት ሁሉ መደረግ የሚገባው መጀመሪያ በካህን (በቄስ) አማካሪነት መጀመር በፍጻሜውም ማስባረክ ተገቢ ነው ። ይህማ ባይሆን ኖሮ ጌታችን በሠርጉ ቤት ተገኝቶ ባልባረከም ፣ በረከትም ባልሰጠም ነበር ።

እንግዲህ በአጠቃላይ ይህ ዕለት ጌታችን አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርቶስ የመጀመሪያውን ተአምር ያደረገበት ነውና ዛሬም ከሕጉና ከሥርዓቱ የራቀውን ዓለም ታርቆ ከታዘዘው መቅሠፍት እንዲሠውረው እንጸልያለን ።

ዲ/ቤዛ ዓለሙ